# ለቃጠሎ ጉዳቶች የመጀመሪያ
# እርዳታ



## በማህበረሰብ ደረጃ ለሚሰሩ የጤና ሰራተኞች
## መመሪያ መጽሐፍ

Interburns

አርማዎን እዚህ ጋር ያስገቡ

ቃጠሎ ምንድን ነው?

ቃጠሎ ማለት አንድ ሰው ላይ በሙቀት፣ ኤሌክትሪክ ወይም ኬሚካል ምክንያት የሚደርስ ማንኛውም አይነት ጉዳት ነው። የቃጠሎ ጉዳቶች **ከቀላል በቤት ውስጥ የሚታከም** እስከ በጣም **ከባድ አስቸኳይ ህክምና** በሆስፒታል የሚያስፈልገው ድረስ ሊለያይ ይችላል ፤ እናም በአንዳንድ ከባድ ሁኔታዎች ሞት ሊያስከትል ይችላል።

**እንደ የማህበረሰብ ጤና ሰራተኛ** ቀላል እና ከባድ ቃጠሎዎችን መለየት መቻል ጠቃሚ ችሎታ ነው። ከዛም አንድ ቃጠሎ በጤና ተቋምዎ መታከም እንደሚችል ወይም ከበድ ያለ ሲሆንና ወደ ሆስፒታል መላክ እንዳለበት ያውቃሉ።

በዚህ መመሪያ መጽሐፍ የቃጠሎ ታካሚ ሲያጋጥምዎ ተገቢ ህክምና እንዲያዘጋጁ፣ እና ታካሚው ወደ ሆስፒታል ይሂድ አይሂድ የሚለውን እንዲያውቁ መፈለግ ያለብዎትን በጣም አስፈላጊ የሚባሉ ምልክቶች እናያለን።

ለቃጠሎ ታካሚ መጀመሪያ መገምገም ያለብዎት **የት** መታከብ እንዳለበት ነው።



- ቤት መታከም ይችላል?
- በጤና ተቋም መታከም ይችላል?
- ለህክምና ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም መሄድ አለበት?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረድዎ ብዙ ምክንያቶች አሉ፣ ነገር ግን በጣም አስፈላጊዎቹ እነዚህ ናቸው:



- → የቃጠሎው መጠን
- → የቃጠሎው አይነት
- → በቃጠሎው የተጎዳው የሰውነት ክፍል

**ይህ መጽሐፍ በእነዚህ ምክንያቶች መካከል ያለው ልዩነት የታካሚውን የህክምና ሂደት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ያስረዳል።**

## የቃጠሎ አይነቶች

አምስት ዋና የቃጠሎ ምንጮች አሉ:



**የነበልባል ቃጠሎዎች:** እነዚህ በእሳት የሚፈጠሩ ቃጠሎዎችን ያጠቃልላሉ፣ ለምሳሌ ከማገዶ እሳት፣ የጋዝ ማሞቂያ፣ የበአል ርችቶች እና በቤት ውስጥ የሚከሰቱ የእሳት አደጋዎች።



**የፈላ ነገር ቃጠሎዎች:** እነዚህ በትኩስ ፈሳሾች የሚፈጠሩ ቃጠሎዎች ናቸው፣ ለምሳሌ ከፈላ ውሀ፣ ሻይ፣ ቡና፣ ወተት እና ሾርባ።



**የትኩስ ገጽታ ቃጠሎዎች:** እነዚህ የሚያቃጥሉ ነገሮችን በመንካት የሚፈጠሩ ቃጠሎዎችን ያጠቃልላሉ፣ ለምሳሌ ትኩስ የወጥ ቤት እቃዎች ወይም ብረት።



**የኤሌክትሪክ ቃጠሎዎች:** እነዚህ በኤሌክትሪክ የሚፈጠሩ ቃጠሎዎችን ያጠቃልላሉ፣ ለምሳሌ ከፍተኛ-ቮልቴጅ የኤሌክትሪክ ገመዶች፣ የኤሌክትሪክ አእታሮች እና መብረቅ።



**የኬሚካል ቃጠሎዎች:** እነዚህ ጠንካራ ኬሚካሎች በቆዳ ላይ ሲፈሱ የሚፈጠሩ ናቸው። ለምሳሌ በቤት ውስጥ የሽንት ቤት ማጽጃዎች፣ ፀረ-ተባዮች፣ እና በባትሪ ውስጥ ያሉ ኬሚካሎች፤ የአሲድ ጥቃቶችም የኬሚካል ቃጠሎ በመባል ይታወቃሉ።

## ታካሚውን መቼ መላክ እንዳለብን እንዴት ማወቅ ይቻላል

**'መላክ' ማለት ታካሚውን ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም ፍላጎታቸው በጤና ኬላው ሊሟላ ስለማይችል በተለይ በቃጠሎ ህክምና ልዩ ባለሙያተኛ ወደሆነ ማስተላልፍ ማለት ነው።*

ቃጠሎው ከባድ ከሆነ ታካሚው መላክ አለበት።
**ቃጠሎ ከባድ መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻላል?**
ያስታውሱ
ሀ) አንድ ሰው ለቃጠሎው መነሻ ለረጅም ለረጅም ጊዜ በተጋለጠ ቁጥር ጉዳቱ የባሰ ይሆናል፣ እና
ለ) ከቅፕዳ ጋር ንክኪ የሚኖረው ገጽታ/ፈሳሽ/ነበልባል ትኩስ በሆነ ቁጥር ጉዳቱ የባሰ ይሆናል።

የቃጠሎን ከባድነት መለየት አዳጋች ቢሆንም ለመሆሰን እንዲረዱዎ መመልከት ያለብዎት የተወሰኑ ነገሮች አሉ:

- **አነስተኛ ቃጠሎ** የተጎዳው ቆዳ ላይ ቀይ መሆንን ይፈጥራል፣ እና መጀመሪያ ላይ እርጥብ ይመስላል። የዚህ አይነት ቃጠሎ በአብዛኛው በጣም ያማል። የዚህ አይነት ቃጠሎ የሰውነትን ትንሽ ክፍል ብቻ ካጠቃ፣ ለምሳሌ ክንድ ላይ፣ በጤና ኬላ ወይም በቤት ውስጥ ሊታከም ይችላል። የዚህ አይነት ቃጠሎ የሰውነትን ትልቅ ክፍል ከሸፈነ፣ ለምሳሌ ሙሉ እጅና እግር፣ ወይም የእጅን፣ የእግርን ወይም የፊትን አብዛኛውን ክፍል፣ ታካሚው ወደ ከፍትኛ የጤና ተቋም መላክ አለበት።

- **ከበድ ያሉ ቃጠሎዎች** ደረቅ ብለው ይታያሉ፣ እና አረፋ መሰል ነገር እና እብጠት ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ቃጠሎዎች ምንም እንኳን ከበድ ቢሉም ለታካሚው ህመሙ ያነሰ ነው። አብዛኞቹ የዚህ ቃጠሎ ታካሚዎች ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም መላክ ይኖርባቸዋል። ትንሽ የሰውነት ክፍል የተጠቁ ታካሚዎች፣ ለምሳሌ የሳንቲም መጠን ያላቸው ብቻ በጤና ኬላው ሊታከሙ ይችላሉ።

- **በጣም ከባዱ የቃጠሎ አይነት** የተቃጠለ እና ነጭ ሆኖ ይታያል። ለመንካት ደረቅ እና ለጉዳቱ ምንም አይነት የህመም ስሜት የለውም። የዚህ ይነት ቃጠሎ ወደ ሆስፒታል መላክ አለበት።

## ታካሚውን መላክ እንዳለብዎት እንዲወስኑ የሚረዱ ሌሎች ምክንያቶች

ያስተውሱ፣ በጣም ቀላል ቃጠሎዎች በጤና ኬላው ሊታከሙ ይችላሉ፣ እና በጣም ከባድ ቃጠሎዎች ወደ ከፍተኛ ተቋም መላክ ይኖርባቸዋል።

እነዚህ ታካሚዎ መላክ ያስፈልገዋል አያስፈልገውም የሚለውን እንዲወስኑ የሚረዱ የተወሰኑ ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው።

- ቀላል ቃጠሎ ስስ ክፍል ላይ ከሆነ ታካሚውን መላክ ይሻላል፤ ምንም እንኳን ለመላክ የሚያደርስ ከባድ መሆኑን እርግጠኛ ባይሆኑም እነዚህ ክፍሎች የባሰ የህክምና ውስብስብነት ሊፈጥሩ ይችላሉ።



  - **'ስስ ክፍሎች' ምንድን ናቸው?**: ራስ፣ አንገት፣ መገጣጠሚያዎች፣ እጆች፣ ፊት፣ ሆድ እና የመራቢያ አካላት።



- ታካሚው በጣም ወጣት ወይም በጣም አዛውንት ከሆነ ታካሚውን መላክ ይመረጣል ጉዳቱ በጣም ቀላል እስካልሆነ ድረስ።

- ታካሚው ምንም ወላጅ ከሌለው የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ሁሉ ማግኘቱን ለማረጋገጥ መላኩ የተሻለ ሊሆን ይችላል።




- ቃጠሎው ቀላል ሆኖ ግን ብዙ የሰውነት ክፍል ከሸፈነ መላክን ከግምት ውስጥ ያስገቡ።

  - **የሰውነት 'ብዙ' ክፍል ምንድነው?**: ለምሳሌ፣ ሙሉ እጅና እግር፣ የጀርባ እና/ወይም ደረት በጣም ሰፊ ቦታ፣ የእጅ አብዛኛው ቦታ፣ የእግር አብዛኛው ቦታ።

- ታካሚው ፊቱ ከተቃጠለ፣ ወይም የመተንፈስ ጉዳት ካሳየ (የአየር መተላለፊያ ወይም የሳንባ ጉዳት) መላክ ይኖርበታል።

  - **የመተንፈስ ጉዳት ምልክቶች ምንድን ናቸው?**: ሳል እና አክታ፣ የሚያሳክክ ጉሮሮ፣ የመተንፈስ ችግር፣ የደረት ህመም ወይም ጥብቅነት፣ ራስ ምታት፣ የአይን መውጋት



- ቃጠሎው የኬሚካል ወይም የኤሌክትሪክ ከሆነ ሁልጊዜ ይላኩ - የቃጠሎው መጠን ምንም ይሁን ምን።



- ቁስሉ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ውስጥ መዳን ካልጀመረ፣ ወይም በበሽታ የተያዘ ከመሰለ ታካሚው መላክ አለበት።

ታካሚው በወሳኝ ሁኔታ ውስጥ ከሆነ እና አስቸኳይ የህይወት ድጋፍ የሚያስፈልገው ከሆነ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ሆስፒታል መላክ አለበት።

## የመጀመሪያ ምላሽ እና የመጀመሪያ እርዳታ

በጉዳቱ ቦታ ላይ ከሆኑ መጀመሪያ **የቃጠሎውን መንስኤ** ለምሳሌ እሳቱን ያጥፉ፣ ትኩሱን ነገር ያስወግዱ። አንድ ሰው በእሳት ከተያያዘ ነበልባሉን ለማጥፋት "***እንዲቆም፣ መሬት እንዲወርድ እና እንዲንከባለል***" ይመከራል።



ከዚያ **ጊዜውን የጠበቀ** የመጀመሪያ እርዳታ መደረግ አለበት። የመጀመሪያ እርዳታ ለመስጠት አነስተኛ መዘግየት መኖሩን ማረጋገጥ የታካሚውን ማገገም፣ ውስብስብነትን ለመቀነስ፣ እና ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ጠባሳ እና ኢንፌክሽንን ለመከላከል ይረዳል። በሁሉም ህክምና ወቅት ታካሚውን ዘና ለማድረግ **የቻሉትን ያህል ረጋ ብለው እና ማበረታታት** አለብዎት።

**<u>የመጀመሪያ እርዳታ ደረጃዎች:</u>**



- በነበልባል/ሙቀት ቃጠሎ ጊዜ ቃጠሎውን ለማቀዝቀዝ እንዲረዳ ለተከታታይ **20 ደቂቃዎች** የ ፍል ላይ ንጹህ ውሀ መፍሰስ አለበት።

- በኬሚካል ቃጠሎ ጊዜ **ኬሚካሎቹን ለማስወገድ/ለማፍዘዝ** ቃጠሎውን በፈሳሽ ወሀ ማጠብ አስፈላጊ ነው። ተጨማሪ የቆዳ መቆጣት እንዳይፈጠር ውሀው ከሰውነት ላይ መንጠባጠቡን ያረጋግጡ፡ ለምሳሌ ኬሚካሉ ራስ ላይ ከሆነ ውሀ ወደ አይን ውስጥ ጠብ እንዳይል ተጨማሪ ጉዳት እንዳያደርስ ያድርጉ።

  **ታካሚውን መላክ ካላስፈለግዎ እና የቃጠሎ ጉዳቱ በጤና ኬላው መታከም ከቻለ እነዚህ ቅደም ተከተሎች ለታካሚው ጥሩ ህክምና እንዲሰጡ ይረዳዎታል፡**

- ቁስሉን በመለስተኛ ሳሙና እና ንጹህ ውሀ ያጽዱ።

- **ሁለት ድርብ** ማልበሻ ያድርጉ። የመጀመሪያው ልባስ በቁስሉ ውስጥ እርጥበትን ለማስቀመጥ እና ልባሱ ከቆዳ ጋር እንዳይጣበቅ እንደ **ቫዝሊን ጎዝ ማልበሻ** የማያጣብቅ መሆን አለበት። ሁለተኛው ልባስ ከቁስሉ የሚወጣን ማንኛውንም ፈሳሽ ለመምጠጥ እንዲረዳ **ውሀ-ከሚመጥ ጨርቅ የሚሰራ ወፍራም ማልበሻ** መሆን አለበት።

- በግምት **በየ3-4 ቀኑ** ወይም አሁን ያለው ሲረጥብ አዲስ ማልበሻ ይስፈገልጋል። ይሁንና በበሽታ የተያዘ ቁስል በየቀኑ የማልበሻ መቀየርን ይጠይቃል። **በበሽታ የመያዝ ምልክቶች**፡ ቁስሉ በጣም ህመም ካለው፣ መጥፎ ሽታ መሸተት ከጀመረ፣ ወይም ከቃጠሎው ቦታ መግል መውጣት ከጀመረ። ቁስሉ በበሽታ ከተያዘ ከሆስፒታል አንቲባዮቲክስ ሊያስፈልግ ስለሚችል ታካሚው መላክ አለበት።

## በቃጠሎ የመጀመሪያ እርዳታ እና የማልበሻ እንክብካቤ ላይ ተጨማሪ መረጃ

በአንዳንድ ማህበረሰቦች እንደ የላም እበት፣ የጥርስ ሳሙና፣ አፈር ወ.ዘ.ተ. በቃጠሎ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል። ይሄ በቁስሉ ላይ ኢንፌክሽን ስለሚፈጥር ብሎም ህክምናውን ስለሚያወሳስብ ይህንን **አለማድረግ** ወሳኝ ነው።

ታካሚውን ከመንካትዎ በፊት እጆችዎን በደንብ እና በየጊዜው መታጠብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ይሄ የጀርሞችን ስርጭት ያቆማል እና የኢንፌክሽን የመፈጠር እድልን ይቀንሳል።

ታካሚው ሊሰማው የሚችል ማንኛውም አይነት አካላዊ አለመመቸትን ለመቆጣጠር እንዲረዳዎ እንደ ፓራሴታሞል ያሉ የህመም ማስታገሻዎችን ይጠቀሙ። መረጋጋትና ማረጋገጥ ማንኛውም ሊያጋጥማቸው የሚችል የስነ ልቦናዊ ጭንቀትን ለመቆጣጠር ይረዳል።

ጉዳቱን ለማቀዝቀዝ ንጹህ ውሀ (ፈሳሽ ቢሆን ይመረጣል) ለ **20 ደቂቃ** ያድርጉበት። ይህንን ካደረጉ በኋላ ከተጎዳው ቦታ ላይ ማንኛውንም ጌጣጌጥ ያውልቁ፣ እና ቁስሉን በሁለት ድርብ ንጹህ ማልበሻ ያልብሱት።

የማልበሻ ክፍሉን እና መሳሪያዎቹን በማምከኛ ያጽዱ

ቃጠሎው እጆች ወይም እግር ላይ ከሆነ ጣቶቹን/የእግር ጣቶቹን ነጣጥለው ማልበሶን ያረጋግጡ።



ህጻናትን ሲያክሙ መጫወቻዎችን መጠቀም ወይም መጫወት በህክምና ጊዜ ከሚኖር ማንኛውም ህመም እንደ ማዘናጊያነት በእጅጉ ሊጠቅም ይችላል። በተጨማሪ ወላጆች በክፍሉ ውስጥ መኖር እጅግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።



ጉዳቱ በ 2 ሳምንት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ካልተሻሻለ ታካሚው ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም መላክ አለበት።

ታካሚው አንዴ ከመጀመሪያ ጉዳቱ ከታከመ በኋላ **በሚመጡት ሳምንታት ጥሩ እንክብካቤ እንዴት ሊሰጡት ይችላሉ?**

ህክምናውን ሲያቅዱ እና ሲያደርሱ እርስ በእርስ መረዳዳት እና መተጋገዝ እንዲችሉ፣ ብሎም የጥሩ ህክምና ውጤቶችን ለማረጋገጥ **ታካሚውንና ቤተሰቡን አብረው ማጠቃለልዎን** ያረጋግጡ።

በጤና ኬላ በሚያክሙበት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ታካሚዎች ላይ **የኢንፌክሽን ምልክቶችን** መከታተል አስፈላጊ ነው። ጉዳቱ በበሽታ ተይዟል ብለው ከጠረጠሩ ታካሚውን በተቻለ ፍጥነት መላክ አለብዎት።

**ኢንፌክሽን እንዴት መለየት ይቻላል:**

ከፍ ያለ የሙቀት መጠን

በእረፍት ላይ እንኳን ከፍ ያለ የልብ ምት

የጉዳቱ ቦታ ላይ መግል

**ጥሩ አመጋገብን ያረጋግጡ**

ከአመጋገብ እይታ አንጻር የተመጣጠነ ምግብ እጥረት የመዳን ሂደቱን ስለሚያዘገየው ከጉዳት በኋላ በተቻለ መጠን ታካሚው ሙሉ እና የተመጣጠነ ምግብ መመገብ አለበት። በተጨማሪ ቃጠሎዎች ታካሚውን ለድርቀት ሊዳርጉ ይችላሉ፣ ስለዚህ ታካሚውን ፈሳሽ እንዲጠጣ ማበረታታት አለብዎት፤ በተለይ የሚገኝ ከሆነ በአፍ የሚወሰድ የእርጥበት ውህድ። ተቋሙ ካልዎት አንዳንድ ታካሚዎች ጠብታ ሊፈልጉ ይችላሉ።



**ጠባሳ**

አንድ ታካሚ ለመዳን ከሶስት ሳምንት በላይ የሚወስድ ከባድ ቃጠሎ ካለው ጠባሳ የመፍጠር እድሉ ከፍተኛ ነው። ለከባድ ቃጠሎዎች ጠባሳው ጎልቶ ሊወጣ ይችላል።

ከከባድ ቃጠሎ በኋላ ታካሚው የተለየ እንደሆነ መታየት እና መሰማትን እንዲያስተካክል ቤተሰብ፣ ጓደኞች እና ማህበረሰብ ማገዝ አስፈላጊ ነው። ዝምተኛ እና ገለልተኛ ሊሆኑ ይችላሉ፣ በተለይ ጠባሳው የሚታይ ከሆነ ወይም ቃጠሎው በተወሰነ ደረጃ የአካል ጉዳትን ካስከተለ። ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ተንከባካቢ እና አዎንታዊ አመለካከት ታካሚው በቃጠሎው ምክንያት በሚያጋጥመው ስነ ልቦናዊ ጭንቀት ውስጥ በመርዳት ትልቅ ለውጥ ሊፈጥር ይችላል።

